በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ፤252993

7/2/2017

ዳኞች ሺመክት አሰፋ

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፦ሁሴን መሃመድ ወኪል መሃመድ ገበየሁ - አልቀረቡም

ተጠሪ፦የደጎሎ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአማራ ክልል በጃማ ወረዳ ፍ/ቤት ሆኖ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በቀን 30/10/2014 ዓም ያቀረቡት ክስ በዳጎሎ ከተማ ውስጥ በምስራቅ መንገድ፤በምእራብ አሰገድ ሙህየ፤በደቡብ መንገድ፤በሰሜን ማርቆስ ሃይሉ የሚያዋስኑት 250 ካ ሜ ቦታ ያለኝ ሲሆን በተጨማሪነት በማስፋፊያ መልክ የያዝኩት 111.43 ካሜ ይዞታ አለኝ፡፡በዚህ ይዞታ ላይ ምንም አይነት የአፈጻጸም ክስ ሳይቀርብብኝ በዋና ይዞታዬ በስተሰሜን አቅጣጫ 20 ካሜ ያህል በመግፋት በአጥሬና ዲሽ ላይ ተጠሪ ጉዳት አድርሶና አፍርሶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይዞታውን በመውሰዱ ቦታውን እንዲመልስ፤እንዲሁም አጥርና ዲሽ ላይ ለደረሰ ጉዳት በድምሩ ብር 2000 (ሁለት ሺ ብር) ወጪ ኪሳራ ተጨምሮ እንዲከፈል ተብሎ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ካለው 250 ካሜ ይዞታ ውጪ የመንግስት ይዞታ ጨምሮ በማጠሩ እንዲያፈርስ ሲጠየቅ ፍቃደኛ ባለመሆኑ ክስ ቀርቦ በመ/ቁ፤0127393 አልፎ የያዘው 130 ካሜ ይዞታ እንዲያፈርስ በፍ/ቤት ተወስኖበታል፡፡ከዚህ ውጭ መሃመድ አራጋው የተባለ ግለሰብ በሊዝ የገዛው ቦታ ስለሆነ ጨምሮ ያጠረውን አቶ መሃመድ አራጋው ተጠሪን ከሶ ተወስኖለት በአፈጻጸም ከህግ ውጪ የታጠረውን አጥር አፍርሰን አጥሩንና ዲሹ ከማስረከብ ውጪ ከአመልካች የወሰድነውም ሆነ ያለፍንበት ይዞታ የለም በማለት ተከራከረ፡፡ የስር ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ማስረጃ መርምሮ የአመልካች ምስክሮች ከሰሜን አቅጣጫ 20 ካሜ ያህል ተጠሪ ማለፉን አላስረዱም በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ እንዲሆን ወሰነ፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ ተሰምቷቸው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ እስከ አማራ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንተዋል፡፡

ይህ ፍ/ቤትም የሰበር አቤቱታውን እንደመረመረው ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ ተጠሪ ድንበር ገፍቶ ይዞዋል በሚል አመልካቹ ክስ ያቀረቡበት አቅጣጫ እና መጠን በማስረጃ ከተረጋገጠው አቅጣጫ እና መጠን የተለያየ ነው በሚል አመልካቹ እንደክሱ አላስረዳም ተብሎ ክሱ ውድቅ የመደረጉን አግባብነትና እና ተያያዥ ቅሬታ ነጥቦች አንጻር የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖር ለመመርመር ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በማስቀረብ አከራክሮዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የቀረበውን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ፤በዚህ ችሎት ከተያዘው ጭብጥና እና ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች 20 ካሬ ሜትር ድንበር ታልፎ አጥርና ዲሽም ላይ ጉዳት ደረሰ ያሉት ከሰሜን አቅጣጫ ነው፡፡ በሰሜን አቅጣጫ ደግሞ አመልካች ከራሳቸው ድንበር አልፈው የመንግስትና ለሌላ ሰው የተመራ ቦታ በመያዛቸው በፍርድ ቤት የተፈረደባቸው መሆኑና የፈረሰው አጥርና የተነሳው ዲሽም በዚሁ አልፈው በያዙት ቦታ መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አመልካች አልፈው በያዙት ቦታ ያጠሩት አጥር ሲነሳ የሳቸው የሆነ ቦታ ተጨምሮ የተወሰደባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ አላስረዱም፡፡ በምስራቅ አቅጣጫ አመልካች ድንበር ታልፎ አጥር የተነሳባቸው ስለመሆኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ያቀረቡት ክስ የለም፡፡እንዳውም የተከሳሽ ምስክሮች በምስራቅ አቅጣጫ አመልካች ከአጥር ውጪ የሚቀራቸው 50 ሳ.ሜ ይዞታ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ይህ ማለት አመልካች በምስራቅ አቅጣጫ አጥራቸውን ሲያጥሩ 50ሳ.ሜ ለቀው ስለማጠራቸው የሚጠቁም ሲሆን፤ባለሙያ ያቀረበውም አመልካች ከምስራቅ አቅጣጫ 12.5ካ.ሜ ይዞታ እንደቀራቸው ነው፡፡በዚህ ቦታ ላይ ደግሞ ተጠሪ አጥር አፍርሶ ድንበር አለፈ ተብሎ ስላልተከሰሰ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተገቢ እና ህግን የተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም ከዚህ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

- የአ/ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0338205 በሰኔ 12 ቀን 2015 አ.ም የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
- የዚህን ፍርድ ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !